# የዜጎች መድረክ

ቅፅ 1 ቁጥር 18 ህዳር 4 ቀን 2012 ዓ.ም
በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የትምህርት ፖሊሲ ቀረጻ የትኩረት ነጥቦች



## ርዕሰ አንቀጽ

# ህዳሴ ግድብን እንደግፍ፣ በንቃትም እንጠብቀው!

በተጀመረ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ተጠናቆ፤ ሥራውን ጀምሮ፤ በሀገራችን ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ሙሉ በሙሉ ያሟላል፤ ከዚያም አልፎ ለሌሎች ሀገሮችም የሚተርፍ ኃይል ያመነጫል፤ "ሻማ የሚለኮሰው ለልደት በዓል ብቻ ይሆናል"፤ "ኩራዝና ፋኖስ ሙዚየም ይገባሉ";፤ "ድህነት ተረት ይሆናል" በሚሉ የተጋነኑ የተስፋ ቃላት የተጀመረው የህዳሴ ግድብ በወቅቱ የነበሩ ሹማምንት ዋነኛ የሀብት መመዝበሪያ መሣሪያ ሆኖ ነበር።

የለውጡ አመራር ሥልጣን ከያዘ ወዲህ አንፃራዊ በሆነ መንገድ ከፍተኛ መሻሻል ከታየባቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ ቀዳሚው ይህ የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ነው ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ለዚህ መሻሻል ለመንግሥትና ለፕሮጀክቱ አዳዲስ አስተዳዳሪዎች አክብሮቱንና አድናቆቱን ይገልፃል።

ይህ ማለት ግን አሁን የህዳሴ ግድብ ችግሮች ተቃለዋል፤ ሁሉም ነገር ተስተካክሏል ወይም ከእንግዲህ የሚያሳስብ ጉዳይ የለም ማለት አይደለም። እንደሚታወቀው ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ከራሳቸው ብቻ ሳይሆን ከሕፃናት ልጆቻቸው የዕለት ጉርስ ቀንሰው አዋጥተዋል። ኢትዮጵያዊያን ለዚህ ግድብ ይህን ያህል ዋጋ የከፈሉት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ስላለው ብቻ አይደለም፤ ከዚያ ያላነሰ ለብሔራዊ አንድነትና ክብር ዋጋ ያለው ፕሮጀክት ስለሆነ ጭምር ነው። በመሆኑም ይህ ዋጋ የተከፈለበት ፕሮጀክት ፍፃሜ ማድረስ ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት መሆኑ የፕሮጀክቱ አስተዳዳሪዎች ብቻ ሳይሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲያስታውሱ ማድረግ ያስፈልጋል።

ኢዜማ የህዳሴ ግድብ መሳካት ያለውን ሀገራዊ ፋይዳ በጥልቀት ይገነዘባል። ፕሮጀክቱ በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ ከሚኖረው ተጽዕኖ ባላነሰ (ምናልባትም በበለጠ) የሀገር ደህንነት (ሴኩሪቲ) እና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ገጽታዎች እንዳሉትም ኢዜማ ይገነዘባል። በዚህም ምክንያት ለህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት መሳካት የበኩሉን እገዛ ያደርጋል። ከዚሁ ጋር ግን አጽንዖት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች መኖራቸውን ያስገነዝባል።

ከሁሉ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በፕሮጀክቱ አስተዳደር ላይ እምነት እንዲያሳድር እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። በንብረትና ፕሮጀክት አስተዳደር ላይ እየተደረጉ ያሉ ለውጦች በየጊዜው በቃላት መገለጽ፤ በተግባር መታየት ይኖርባቸዋል። አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የፕሮጀክቱ ባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው በተቻለ መጠን ግልጽነት እና ጥብቅ የሆነ ተጠያቂነት እንዲኖር መሠራት ይኖርበታል።

በህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ላይ ቀና ያልሆነ ስሜት ያላቸው ኃይሎች ጥቂት እንዳልሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥም አቅም ያላቸው አካላት ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል። እነዚህ ኃይሎች ፕሮጀክቱን ለማስተጓጎል ምን ዓይነት እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ አስቀድሞ በመገመት ቀዳዳዎችን መዝጋት ይገባል። በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ እየተስፋፋ ያለው ግጭት ከዚህ ፕሮጀክት ጋር ዝምድና ይኖረው እንደሆነ መጠየቅ፣ መመርመር፣ መፈተሽና ምላሽ ማግኘት ይገባል።

የህዳሴ ግድብ ፕሮጀክት ችግር ውስጥ የከተታቸው ወይም ሊከታቸው የሚችሉ ዓለም ዓቀፍ ግንኙነቶች ቢኖሩም ለአዳዲስ ዓለም ዓቀፍ ግንኙነቶች አመቺ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል ብሎ ኢዜማ ያምናል። በተለይም የአፍሪቃ ቀንድ ሀገራትን ለማስተባበር ህዳሴ ግድብ ለመልካም ጉርብትና ዲፕሎማሲ ግብዓት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። ግድቡን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በሀገራት መካከል የሚደረጉ ውይይቶች እና ስምምነቶች ለሕዝብ እንዲገለጹ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን፡፡

ኢዜማ ህዳሴ ግድብን እንደግፍ፣ ለመልካም ጉርብትና እንጠቀምበት፤ ለኢትዮጵያና ሕዝቧ በጎ ለማይመኙ ኃይሎች መሣሪያ እንዳይሆን ደግሞ ነቅተን እንጠብቅ ይላል።

# ‹ < <ኢዜማ መንግሥትነቱ ለመረጡትና ለደጋፊዎቹ ብቻ አይደለም፤ መንግሥትነቱ ለአጠቃላይ ሕዝቡና ለማይወዱት ጭምር ነው> > ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)

ሕዳር 04 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)




የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) እሁድ ጥቅምት 30 ቀን 2012 ዓ.ም በምርጫ ወረዳ 1/9 ካሉ ደጋፊዎቹ፣ አባላቱና ነዋሪዎች ጋር በሰሜን ሆቴል ውይይት ማካሄዱን የምርጫ ወረዳ 1/9 ሰብሳቢ ሙሴ መስፍን ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

ውይይቱ ማካሄድ ያስፈለገው የኢዜማን ፕሮግራም ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ወቅታዊው የሀገሪቷ ሁኔታ ላይ የኢዜማ አቋም ምን እንደሆነ ለማብራራት፣ በኢዜማና በለውጡ ኃይል መካከል ያለውን ግንኙነት ለማብራራት፣ የኢዜማ መሰረታዊ አደረጃጀቶችን ግልፅ ለማድረግና እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር በአካባቢውና በነዋሪዎቹ በመረጡት ሰው መተዳደር እንዳለበትና ይህን እውን ለማድረግም ኢዜማ ምን እየሠራ እንዳለ ግልፅ ለማድረግ መሆኑን ሰብሳቢው አስረድተዋል፡፡

ከስብሰባው ተሳታፊዎች ኢዜማ የሚከተለው ርዕዮት ዓለም ምንድን ነው? ፓርቲው በሚሰጠው መግለጫም ሆነ የፓርቲው መሪ በግላቸው የለውጡን ኃይል በመደገፍ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ማድረስ ይገባል ይላሉ፡፡ ይህ ጉዳይ በግልፅ ቢብራራልን? ኢሕአዴግ በአዲስ አስተሳሰብና በርዕዮት ዓለም ተዋህጄ እመጣለሁ እያለ ነው፡፡ በዚህ ላይ የኢዜማ ምን አስተያየት አለው? ኢዜማን አሀዳዊ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ለእነዚህ ወገኖች ምን ምላሽ አላችሁ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸውንና ለጥያቄዎቹም መሪው ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) እና ሊቀመንበሩ የሺዋስ አሰፋ ምላሽ መስጠታቸውን ሰብሳቢው ጠቁመዋል፡፡

በስብሰባው ላይ መሪው ብርሃኑ ነጋ «ኢዜማ ተመርጦ መንግሥት ከሆነ መንግሥትነቱ ለመረጡትና ለደጋፊዎቹ ብቻ አይደለም፤ መንግሥትነቱ ለአጠቃላይ ለሕዝቡና ለማይወዱት ጭምር ነው፡፡ ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተዳድር መንግሥት ነው የሚሆነው፡፡ ለዚህም ነው ዘመን ተሻጋሪ ይሆናል ብለን የምናምነው፡፡ ፓርቲውን ያልተቀላቀላችሁ ተቀላቀሉ፤ አካባቢያችሁንም ጠብቁ፡ ፡ አካባቢያችሁን በትክክለኛ መንገድ ሊያስተዳድሩ የሚችሉ ሰዎች ለውድድር አቅርቡ» ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ አያይዘውም «መድረስ የምንፈልግበት ስትራቴጂክ ግባችን ይህቺ ሀገር በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ዴሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን ማድረግ ነው» ብለዋል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema


የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 4 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የትምህርት ፖሊሲ ቀረጻ የትኩረት ነጥቦች

## (ለውይይት መነሻ የቀረበ አጭር ጽሁፍ)

### 1.መግቢያ

በዓለማችን ላይ ሀገራት የትምህርት ሥርዓታቸው እንዲሳካ ለትምህርት ፖሊሲ ሠፊ ትኩረት ይሠጣሉ፡፡ በተለይም የሉላዊነት ተጽዕኖ እየበረታ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የትምህርት ፖሊሲ በዜጎች ላይ ስለሚኖረው አጠቃላይ ተጽዕኖ በጥልቀትና በጥሞና ማጥናት አስገዳጅ እየሆነ መጥቷል፡፡ በአንጻሩ የበርካታ ሀገራትን የትምህርት ፖሊሲ ዝግጅት እና ገፊ ሁኔታዎችን (pushing factors) በመለየት ሂደት ሰፊ የግንዛቤ ጉድለት እንደሚስተዋል ጥናቶች ያስገነዝባሉ፡፡

የሀገራችን ተሞክሮም ከዚህ ያልተለየ በመሆኑ ለትምህርት ፖሊሲ ዝግጅት እና ለፖሊሲ መሻሻል ገፊ ሁኔታዎችን (pushing factors) በጥሞና መመልከት ተገቢ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ከዚህ በመነሳት በትምህርት ፖሊሲ ዝግጅት ወቅት መሰረታዊ ማዕቀፎች የሆኑ ጉዳዮችን አንስቶ መመካከር ተገቢ ይሆናል፡፡ በርከት ያሉ ለትምህርት ፖሊሲ ቀረፃ የሚረዱ የትኩረት ነጥቦች ያሉ ሲሆን በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ ለውይይት መነሻ የሆኑ ጽሑፎች በተከታታይ እየተዘጋጁ ይቀርባሉ፡፡ በዚሁ መሰረት የትምህርት ስታንዳርድ መሰረታዊ አስተሳሰብ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.1.የስታንዳርድ ፅንሰ-ሃሳብ ምንነትና በትምህርት ዘርፍ ያለው አተገባበር

#ስታንዳርድ; የሚለው ፅንሰ-ሃሳብ በቁሙ የጥራት ወይም የብቃት ደረጃን/level of quality or excellence/ ያመለክታል፡፡ የቃሉ አግባብ በግለሰብም ይሁን በተቋም ደረጃ የተቀመጠን የብቃት ወይም ጥራት ደረጃንና ይህንኑ ተከትሎ በመጨረሻ ላይ የሚከናወነውን የግምገማ ሥርዓት ጭምር ያጠቃልላል፡፡ የተቀመጠው ስታንዳርድ እና የግምገማ አሠራሩ በሚተገበርበት የቦታም ሆነ የይዘት ወሰን ወጥ መሆን የስታንዳርድ መለያ ባሕርይ ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል የተቀመጠ ስታንዳርድን መሠረት በማድረግ የተገኘውን ውጤት ለማነፃፀር ያስችላል፡፡ የተገኘው ውጤት ከተቀመጠው የስታንዳርድ ደረጃ ያነሰና ከፍ ያለ የመሆኑ ሁኔታ የተደረሰበትን የብቃትም ሆነ የጥራት ደረጃ ለማየት ከማስቻሉም በተጨማሪ በቀጣይ እንቅስቃሴ/ጥረት ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በትምህርት ሥራም የሚቀመጥ ስታንዳርድ ተመሳሳይ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል የማይታበል ሀቅ ነው፡፡ የትምህርት ስታንዳርድ ለተባባሪ አካላት ሁሉ እንደፍኖተ-ካርታ ከማገልገሉም በላይ ለፖሊሲ አውጭዎችም አቅጣጫ ሊያሳይ እንደሚችል ይታመንበታል፡፡

አሁን ያለንበት የሉላዊነት ዘመን የኢኮኖሚ አወቃቀሩ በትምህርት ልቀት ላይ በእጅጉ የተመሰረተ እና ትምህርት ለሀገራት ስኬት ያለው ፋይዳ ወሳኝ እየሆነ መጥቷል፡፡ በመሆኑም የበለጸገ የትምህርት ሥርዓት በተፈለገበት በአሁኑ ወቅት ሀገራት እና የሚመለከታቸው የትምህርት ዘርፍ ተዋናይ አካላት የትምህርት ስታንዳርድ በማዘጋጀት ይህንን የወቅቱን የመልማት ፍላጎት እያሟሉ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይም እነዚህ የትምህርት ሥራ ልቀትን የሚያግዙ ስታንዳርዶች በየጊዜው ወቅቱን በሚመጥን መልኩ በሥነ-ትምህርት ምርምሮች እየታገዙ መዳበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ የትምህርት ስታንዳርድ ሲባል ዜጎች በተለይም የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች እውቀት ለመቅሰም በሚሠማሩበት የትምህርት ክፍልና እርከን ምን ማወቅ፣ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ተለይቶ የሚቀመጡ የትምህርት ዓላማዎች እና ውጤቶች አካትቶ የሚይዝ ሰነድ ነው፡፡ የትምህርት ስታንዳርድ እንደ አተገባበር ደረጃው መለያየት በዝርዝር ወይም በጥቅል ዓላማ ተቀምጦለት ሊቀረጽ ይችላል፡፡

የትምህርት ስታንዳርድ በትምህርት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት በተግባቦትና ኃላፊነትን በተገቢው መንገድ በመወጣት ረገድ እንዲንቀሳቀሱ በማገዝ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው፡፡ የትምህርት ስታንዳርድ ለአፈጻጸሙ የተቀመጡ መመዘኛ ነጥቦችን አካትቶ የያዘ በመሆኑ በአመዛኙ ወጥነት እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡

የትምህርት ስታንዳርድ ከትምህርት ሥራ ስፋት የተነሳ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ የጽንሠ ሀሳብ አመዳደብ ዝርዝሮችን በመለየት ያብራሩልናል፡፡ ለአብነትም ያህል የትምህርት ስታንዳርድ፣ ሀገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ የትምህርት የሙያ ስታንዳርድ፣ የብቃት ማረጋገጫ ስታንዳርድ ወዘተ… መጥቀስ ይቻላል፡፡

የትምህርት ስታንዳርድ ኅብረተሰቡ ሊያሳካ የሚፈልገውን የትምህርት ይዘት (Curriculum)፣ የማስተማር ስልቱንና (Teaching method) የግምገማ ውጤቱን (Assessment result) አስመልክቶ የምንገልፅበት መንገድ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ግምገማው በቀረበው ትምህርት አማካኝነት ተማሪዎች ያገኙትን የዕውቀት፣ የክህሎት፣ የአመለካከት ውጤትና ምን ያህሉንም በሥራ ሊገልፁት እንደሚችሉ የሚያስረዳ ነው፡፡ በእርግጥ የግምገማው ውጤት በተለያየ መልክ ሊገለፅና የውጤቱ ከፍና ዝቅ ማለትም ከተቀመጠው ስታንዳርድ ስኬት አንፃር ሊመነዘር እንደሚገባው ይታመንበታል፡፡

የትምህርት ግምገማ ስታንዳርድን (Educational Assessment Standard) ስናነሳ ሳንጠቅስ የማናልፋቸው ብዙ ጉዳዮች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹን ከዚህ በታች እንዘረዝራቸዋለን፡፡

### 2.የሥርዓተ-ትምህርት ስታንዳርድ

የሥርዓተ-ትምህርት ስታንዳርድ ልጆች በአንድ በተወሰነ የክፍል ደረጃ ተምረው ሊደርሱበት ስለሚገባ የትምህርትና ዕውቀት ደረጃ የሚያስረዳ ነው፡፡ ለምሣሌ በአሜሪካ ውስጥ የጋራ ስታንዳርድ (Common Standards) ተብለው የተቀመጡት የትምህርት ዓይነቶች ሒሣብና እንግሊዘኛ ናቸው፡፡ ስታንዳርዱን ገላጭ የሆኑ ማብራሪያዎች ቀደም ብለው በሥርዓት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ መምህራኑም (ከመምህራን ጋር በተያያዙ የሚነሱ የስታንዳርድ ጉዳዮችን አስመልክቶ በሌላ ጽሑፍ ይዘን እንቀርባለን) የማስተማር ስልታቸውን ለዚህ ስኬት ያውሉታል፡፡

በመጨረሻም በተቀመጠው የትምህርቶቹ ስታንዳርድ መሠረት ተማሪዎች በደረሱበት የክፍል ደረጃ ተገምግመው በነዚህ

ትምህርቶች ያስመዘገቡት ውጤት እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የተለያዩ ሀገሮች በተወሰኑ ትምህርቶች ላይ ብሔራዊ ሥርዓተ-ትምህርት ስታንዳርድ ቀርፀው በትምህርት ጥራታቸው ላይ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ በእኛም ሀገር ተመሣሣይ ልምድ ቢኖርም በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ብሔራዊ ስታንዳርድ ይኑረን ለሚለው ግን ምሁራኖቻችን ሀገርን በማስቀደም ተወያይተውበት ዕልባት ሊያገኝ ይገባዋል፡፡

## 3.የምዘና ስታንዳርድ

በምዘና ሥርዓት ውስጥ ሶስት ፅንሰ-ሃሳቦች በጣም የተለመዱ ናቸው፡፡ ቅቡልነት (Validity)፣ አስተማማኝነት (Reliability) እና ፍትሀዊነት (Fairness) ናቸው፡፡ በምዘና ሂደት ወስጥ ቅቡልነት የምዘና መሣሪያው ከጅምሩ የተነሳበትን ዓላማ (የዕወቀት፣ የክህሎትና የአመለካከት ችሎታን ለመለካት ወጥኖ ቢዘጋጅ ለማለት ነው) አሳካቷል ወይም አላሳካም ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡ አስተማማኝነት ደግሞ የምዘና መሣሪያው ቢደጋገም ተመሣሣይ ውጤት ስለማምጣቱ መልስ የሚሰጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍትሀዊነት ምዘናው ለሁሉም ተመዛኞች ያለአድልዎ (የጊዜና የልዩ ልዩ ድጋፎች ያለመለያየት) ስለተካሄደበት ሁኔታ መልስ ይሰጣል፡፡ እንደዚሁም የምዘና መሣሪያው ለሁሉም ተደራሽ (የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ) ስለመሆኑም ፍትሀዊነት መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

ለመሆኑ የምዘና ስታንዳርድ የማውጣት አስፈላጊነቱ ለምንድነው? የሚከተሉት ነጥቦች መልስ ይሰጣሉ ብለን እናምናለን፡፡ ይኸውም፡-

- በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ የትምህርት ምዘና ውጤቶችን በመውሰድ በአንድ ወቅት የነበረውን የትምህርት ደረጃ ከሌላው ጊዜ ጋር ለማነፃፀር ያስችላል፡፡
- የትምህርት ምዘና ውጤቶች ለቀጣይ የትምህርትም ሆነ የምዘና ሥራ ግብአት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
- በትምህርት ምዘናው የሚገኘውን ውጤት ተከትሎ ተመዛኙ ስላገኘው የትምህርት ማስረጃ አስተማማኝነት ለመግለፅ ይቻላል፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚካሄድ ምዘና ከዚህ በላይ የተከተሉትን ጥቅሞች ሊያስጨብጥ ካልቻለ ምንም የሚያስገኘው ፋይዳ ሊኖር አይችልም፡፡ በእኛም ሀገር ውስጥ በየደረጃው የሚካሄዱ የሀገርና የክልል አቀፍ የምዘና ስታንዳርዶች የታለመላቸውን ዓላማ ስለማሳካታቸው ጥልቅ ጥናት ተካሂዶባቸው ጉድለታቸው ሊሞላ ይገባል፡፡

## 4.ዓለም-አቀፍ የትምህርት ስታንዳርድ

በመሠረቱ የጋራ የሆኑ ስታንዳርዶች አንዱ ሀገር ከሌላው የሚቀዳቸውና የትምህርት ሥርዓቱን ለማሻሻል የሚያስችሉት ናቸው፡፡ በዓለማችን ብዙ ሀገሮች በተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች (Mathematics, Science, English ወይም Mathematics, Science, and Technology Education) ላይ ብሔራዊ (National) ስታንዳርድ ይጥላሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ አካሄድ የራሱ ጥቅሞች አሉት፡፡ ይኸውም የየሀገራቱ ተማሪዎች ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪነታቸውን፣የት/ቤቶቻቸውን መሻሻል፣ ትምህርቱ ለሁሉም ዜጎች እኩል ዕድል የመሥጠቱንና ለሕዝቦቻቸውም ዝውውር (በሀገርም ውስጥም ሆነ በውጭ) ዋስትና ሊሰጥላቸው እንደሚችል ያምኑበታል፡፡

## 5. ሌሎች የትምህርት ግብአት ስታንዳርዶች

በዚህ ሥር ከትምህርት ግብአቶች ጋር ተያይዞ የሚነሱት ስታንዳርዶች ናቸው፡፡ ትምህርት ቤቶች ከህንፃ ግንባታቸው ጀምሮ በውስጣቸው እስከሚያደራጁት የትምህርት ግብአት ድረስ በስታንዳርድ የታጠረ ነው፡፡ በመሆኑም ከቅድመ-መደበኛ እስከ ዩኒቨርስቲ ባሉት የትምህርት እርከኖች በሙሉ የሚገነቡ ተቋማት ሊያሟሉ ስለሚገባቸው ልዩ ልዩ የህንፃ ክፍሎች ባስገዳጅ ሁኔታ እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡

የዚህም ዋና ዓላማ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ተስማሚ የመማሪያ ማስተማሪ አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ራሱ የትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ቦታ፣ የየክፍሎቹ ቁጥርና ስፋት፣ የቤተ-መጻሕፍት፣ የቤተ-ሙከራ፣ የስፖርት ሜዳ፣ የመፀዳጃ ቤቶች፣ የትምህርት ቤት አጥር፣ ሠሌዳ፣ ወዘተ... ስታንዳርድ ይወጣላቸዋል፡፡ በእርግጥ የዚህ ዓይነቱ ስታንዳርድ ከሀገር ሀገር ሊለያይ ይችላል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር በሕግ በተሰጠው አግባብ መሠረት የትምህርት ስታንዳርዶችን የማውጣት ሥልጣን አለው፡፡ እስከዛሬም የተለያዩ ስታንዳርዶችን አውጥቶ ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ክፍተቶችም ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም አንዳንድ የትምህርት ተቋማት መሥፈርቱን ሳያሟሉ በፌደራልም ሆነ በክልሎች እንዲከፈቱ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሣ የትምህርቱን ጥራት እንዲያሽቆለቁል አድርገውታል፡፡ በዚህ ረገድ በመንግሥትም ሆነ በግል ባሉ ትምህርት ቤቶች በጥራት ዙሪያ ብዙ መሥራት እንደሚገባ መገመት አያዳግትም፡፡

## 6.ማጠቃለያ

የምንኖርባት ዓለም የሥልጣኔ ግስጋሴ እያደር እያደገ በሚሄድ እውቀት ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ስኬትም ከዚሁ እውቀት የሚመነጭ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን የአኗኗር ዘይቤ ተከትሎ ለመራመድ ሳይንሳዊ የትምህርት ሥርዓት መመስረት የግድ ይላል፡፡ የትምህርት ሥርዓትና ፖሊሲም በሚፈለገው ደረጃ መድረሱን ለማረጋገጥ የትምህርት ስታንዳርድ ወሳኝ ግብዓት ሲሆን በትምህርት ፖሊሲ መንደፍ ውስጥ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ሆኖ የተወሰደ ነው፡፡

በሀገራችንም የትምህርት ስታንዳርድ የሚያስቀምጥ ብሔራዊ ተቋም በመፍጠር የትምህርት ስታንዳርድ ሪፎርም እንቅስቃሴ ማካሄድ ይኖርብናል፡፡ በትምህርት ሥርዓታችን ላይ ወሳኝ እርምጃ ካልወሰድን በስተቀር የሀገራችንን ራዕይ ለማሳካት አንችልም፡፡ በመሆኑም ሁሉንም የተባባሪ አካላት የሚያሳትፍ የትምህርት ስታንዳርድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የሚዘጋጀው ስታንዳርድ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያስገኝልን እንደሚችል መታመን አለበት፡፡ ይኸውም፡-

- የትምህርትን ጥራት ሊያሻሽልልን ይችላል፡፡
- የትምህርት ሥራ አፈፃፀማችንን ሥርዓት ባለው መንገድ ለመገምገም ያስችለናል፡፡
- በመንግሥትና በግል ያሉ የትምህርት ተቋማትን ለማቀራረብ ያስችላል፡፡
- ክልል ከክልል እንዲሁም በክልል ውስጥ ጤናማ የትምህርት ውድድር ለማካሄድ ያስችላል፡፡

የትምህርት ስታንዳርድ ከላይ ለመወያያ በተነሣው ውስን ጽሑፍ መነሻነት ዜጎች በተለይም በመስኩ የተሰማሩ ምሁራን ባካበቱት እውቀታቸውና ልምዳቸው ለሀገራችን የሚበጅ የፖሊሲ ግብአት ሃሳብ ያንሸራሽሩ ዘንድ ተጋብዘዋል፡፡

በሀገራችን እነዚህ ስታንዳርዶች እንዴት መተግበር እንዳለባቸው የሚዳስስ ተከታይ ጽሑፍ በሌላ ጊዜ ይዘን እንመለሳለን፡፡

# ኢዜማ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ክልሎች ስልጠና ሊሰጥ ነው።

## “ቀጣዩ ምርጫ ከዚህ በፊት እንደነበረው መሆን የለበትም”

ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ
ኅዳር 4 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አዲስ አበባን ጨምሮ 310 የምርጫ ወረዳዎችን በስራቸው ወደያዙ 22 ዞኖች በመንቀሳቀስ ምርጫን በማስመልከት ሥልጠና የሚሰጥ በ8 ቡድን የተከፋፈለ ግብረ ኃይል ዛሬ ኅዳር 4 ቀን 2012 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ይንቀሳቀሳል፡፡

በሦስት ዋና ዋና ዐብይ ክፍሎች የሚሰጠው ሥልጠና የኢዜማ የምርጫ ዝግጅት እና ምርጫው በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ፋይዳ፣ በቅድመ እና ድኅረ ምርጫ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶች እና እንዴት ማስተናገድ እንደሚገባ እንዲሁም የምርጫውን ውጤታማ ለማድረግ መከናወን ስለሚገባቸው ተግባራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለሥልጠናው ከአዲስ አበባ የሚንቀሳቀሰው ቡድን ሥራውን በ4 ቀን አጠናቆ እንደሚመለስ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ገልጸዋል፡፡

«ቀጣዩ ምርጫ ከዚህ በፊት እንደነበረው መሆን የለበትም» ያሉት የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው በሥልጠናው ላይ በቀጣዩ ምርጫ ኢዜማ አሸናፊ ሆኖ ሊወጣበት የሚችልበትን መንገድ አባሎቹና አመራሮቹ እንዲያውቁ ከማድረግ ባለፈ ኃላፊነታቸውን ተረድተው በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያሳውቅ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የመጀመሪያ ዙር የሆነው ሥልጠና በደቡብ ክልል ወላይታ፣ ከፋ፣ ስልጤ፣ አላባን በመሳሰሉ ቦታዎችን የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም ሰሜን ሸዋ፣ ደቡብና ሰሜን ወሎ፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፤ ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ ዞንና አዲስ አበባን ጨምሮ ሥልጠናው የሚሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

# ኢዜማ በአዲስ አበባ ምርጫ ወረዳ 24 ሕዝባዊ ውይይት አደረገ

ኅዳር 4 ቀን 2012 ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)





የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥቅምት 30 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ በሚገኙ 3 የምርጫ ወረዳዎች ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ፡፡

ምርጫ ወረዳ 24 በተዘጋጀው ሕዝባዊ ስብሰባ የኢዜማ መሪ ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)፣ የኢዜማ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ እንዲሁም ሌሎች አመራሮች በተገኙበት ሕዝባዊ ውይይት የተደረገ ሲሆን በውይይቱ ላይ የኢዜማ አባላት ብቻ ሳይሆን አባል ያልሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችም ተሳትፈው ጥያቄ አቅርበዋል፣ ሃሳብና አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡ በዕለቱ የወረዳ 24 የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ማርታ ደሳለኝ «የዜግነት ፖለቲካ እንዲሰፋ ሁላችንም ተሳትፎ ማድረግ አለብን፡፡ በወረዳችን ያላችሁ ነዋሪዎች በኢዜማ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንድታረጉ እንፈልጋለን፡፡ ሁላችሁም በቻላችሁት መጠን ልታግዙን፤ በዛውም ምክር እንድትለግሱን እንፈልጋለን፡፡» ብለዋል፡፡

ኢዜማ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሀገራችን ላይ እንዲመጣ ከሁሉም አጀንዳዎች በላይ አትኩሮት ሰጥቶ እንደሚሠራ ለተሰብሳቢዎች ያስረዱት የኢዜማ መሪ ብርሃኑ «አሁን ያለው መንግሥት ከዴሞክራሲ ውጪ ሀገር መምራት እችላለሁ ብሎ የሚያስብ አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ይሄን እንዲተገብር ማገዝ አለብን» ብለዋል፡ ፡ ከመድረኩ ለተነሱት የተለያዩ ጥያቄዎችም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡